




# ታላቅ የህዝባዊ ስብሰባ ጥሪ

## ከግንቦት 7 የፍትህ፣የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

ግንቦት7 ንቅናቄ የተፈጠረው የ1997 ኢ.ም የግንቦት ሰባት ምርጫና ከእዚህ ምርጫ በኋላ በሃገራችን ውስጥ የተከሰተውን ሁኔታ በሚገባ በመገምገም ነው፡፡ ይህ ግምገማ በአጭሩ እንዲህ ይላል፡፡
ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ስርአተ መንግስት ለማቆም የሚያስችል የፖለቲካ ብስለት አለው፡፡
ተቃዋሚ ድርጅቶችም በሰለጠን መንገድ ተወዳድረው ስልጣን መያዝ ይችላሉ፡፡
በግንቦቱ ምርጫ የወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ በህዝብ ድምጽ ተሸንፏል፡፡
ወያኔ ግን ሽንፈቱን አልቀበልም ብሏል፡፡
ዜጎችን አሳዷል ቀጥቅጧል አስሯል ገድሏል፡፡
የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችን ጋዜጠኞችን የህዝብ መብት ተሟጋቾችን ወህኒ ወርውሯል፡፡ ድርጅታቸውን አፍርሷል፡፡
የግንቦት 1997 ምርጫ እንደማይደገም በቃልም በድርጊትም አረጋግጧል፡፡
ሁሉንም ሰብአዊ መብቶች ገፏል፡፡ የሃገሪቱን ሃብት ዘረኛ በሆነ መንገድ ለተደራጁ በወያኔ ኢህአዴግ በሚመሩ ኩባንያዎች እጅ ማሰባሰቡን ቀጥሏል፡፡ ሰራዊቱንና ደህንነቱን ከመቼውም በከፋ መልኩ ዘረኛ በሆነ መንገድ አዋቅሯል፡፡
ስልጣን ላይ ለመሰንበት የሃገር ዳንበር ቆርሶ ሰጥቷል፡፡ የጎረቤት ሃገር ወሯል፡፡ ሃገራዊ ክህደት ፈጽሟል፡፡
ከጥፋት እንዲመለስ ተመክሯል፡፡ ተለምኗል፡፡ ምላሹ ተጨማሪ እብሪት ንቀትና ብልግና ሆኗል፡፡
ግንቦት7 የተቋቋመው እንዲህ አይነቱን የአጋዛዙን እብሪት እንዴት እንቋቋማለን የሚል ጥያቄ አንስቶ መልስ ከሰጠ በኋላ ነው፡፡

ግንቦት7 ወያኔ የሰለጠነ ፖለቲካ የማይገባው ድፍን ነገር በመሆኑ፣ እስኪገባው መቀጥቀጥ ወይም መወገድ ይኖርበታል ብሎ ያምናል፡፡

ግንቦት7 ወያኔ ኢህአዴግ በሃራችን በሁላችንም ላይ እየፈጸመ ያለው አዋራጅ ድርጊት እንዲቆም ሰፊ ህዝባዊና ደርጅታዊ ህብረት መፍጠር ተገቢ ነው ይላል፤ ይቻላልም ብሎ ያምናል፡፡

ግንቦት 7 ወያኔ ኢህአዴግ አልበርድ ባለው ጥጋቡ እራሱን አሳብጦ መውጣት ከማይችልበት የቀውስ አዘቅት ውስጥ ተደፍቋል የሚል እምነት አለው፡፡

በእዛው ልክ የወያኔ/ኢህአዴግን እብሪት ተንኮል የድርጅት የገንዘብና የብቃት አቅም ማምከን የሚችል ተቃዋሚ ሊገጥመው ያስፈልጋል ብሎ ግንቦት 7 ያምንል

ግንቦት7 ከኢትዮጵያ ህዝብና ከሌሎች ለዴሞክራሲ፣ ለአንድነት ለፍትህና ለነጻነት ከቆሙ ሃይሎች ጋር በመተባበር ይህንን አቅም በአጭር ግዜ ውስጥ መገንባት ይቻላል ብሎ ያምናል፡፡

እንዴት ተደርጎ የሚል ጥያቂ ካለዎት
አይቻልም የሚል የእርግማን መለእክት ማስተላለፍ ካስፈለገዎ
ግንቦት ሰባቱ እደጊ ተመንደጊ ዘር ይውጣልሽ ብለው ለመመረቅ ከፈለጉ
እንዴት ልርዳህ ላግዝህ ብለው የሚጨነቁ ከሆነ

የግንቦት 7 አመራር አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ የንቅናቄውን አላማና ፕሮግራምለህዝብ ያስተዋውቃሉ። እንዲሁም በወቅታዊና አንገብጋቢ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ይሰጣሉ።

በዚህ ወሳኝ መድረክ ተገኝተው በፖለቲካ ትግሉና የሃገራችንን ህልውና በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል።

| | |
|---|---|
| ቀን | ቅዳሜ 5th July 2008 |
| ሰአት | 12፡30 እስከ 3፡30 PM |
| መሰብሰቢያ አዳራሽ | Marriott Hotel ፣1221 22nd Street,NW, DC 20037 |
| የእለቱ እንግዶች | ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ  አቶ ኤፍሬም ማዴቦ<br>አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ  ዶ/ር ግደይ አሰፋ |
| መግቢያ 30$ | Info: 703 595 64 13 |

www.ginbot7.org